የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ግንቦት ፩ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No. 22
ADDIS ABABA 9th May, 2023

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፴፭/፪ሺ፲፭

የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………ገጽ ፲፬ሺ፯፻፵፰

**Content**

Regulation No. 535 /2023

Community-Based Health Insurance Council of Ministers Regulation...........................Page 14748

**ደንብ ቁጥር ፭፻፴፭/፪ሺ፲፭**

**የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን**

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፴፭/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "**አዋጅ**" ማለት የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፫/፪ሺ፲፬ ነው፣

**REGULATION NO.535/2023**

**COMMUNITY-BASED HEALTH INSURANCE COUNCIL OF MINISTERS REGULATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 31 Sub-Article 1 of the Community-Based Health Insurance Proclamation No.1273/2022.

**CHAPTER ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as a "Community-Based Health Insurance Council of Ministers Regulation No.535/2023".

2. **Definition**

In this Regulation: -

1/ "**Proclamation**" means the Community-Based Health Insurance Proclamation No.1273/2022;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ **"መዋጮ"** ማለት ለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አባልነት ከአባሉ ወይም በአባሉ ስም በሌላ አካል የተከፈለ፣ ከተናጠል ድጎማ እና ከአጠቃላይ ድጎማ የሚሰበሰብ አመታዊ ክፍያ ነው፣

፫/ **"ምክር ቤት"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተቋቋመው የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ብሄራዊ ምክር ቤት ነው፣

፬/ **"መሠረታዊ ቋት"** ማለት በወረዳ ወይም እንደአግባብነቱ በዞን ወይም በክልል ደረጃ ወይም ከነዚህ ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ባለው የከተማ አስተዳደር መዋቅር የተመሠረተ የአባላት መዋጮ ገቢ የሚደረግበት የመጀመሪያ ቋት ነው፣

፭/ **"ክልላዊ ቋት"** ማለት ከክልል በታች ካሉ ቋቶች በሚተላለፍ ድርሻ በክልል ደረጃ የሚመሠረት ቋት ሲሆን በክልል ደረጃ የተመሠረተ መሠረታዊ ቋትን ይጨምራል፣

፮/ **"የመጀመሪያ ደረጃ አሃድ የጤና ተቋም"** ማለት የጤና ኬላ፣ የጤና ጣቢያ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ሲሆን በእነዚህ ደረጃ ያሉ ሌሎች የጤና ተቋማትን ይጨምራል፣

፯/ **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት የተፈጥሮ አደጋ፣ የእርስ በእርስ ግጭት ወይም ጦርነት፣ በመንግስት የተሰጠ ልዩ ትዕዛዝ ወይም ሌሎች ከአስፈጻሚው አካል ቁጥጥር ውጪ የሆኑ እና አስቀድመው ሊገመቱ የማይችሉ ምክንያቶች ናቸው፣

፰/ **"የፌደራል አስፈጻሚ አካል"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመላከተው የኢትዮጵያ የጤና መድኅን አገልግሎት ነው፣

2/ **"Contribution"** means the annual Community-Based Health Insurance membership fee made up of payments made directly by paying members or paid on their behalf, targeted and general subsidies;

3/ **"Council"** means the National Community-Based Health Insurance Council established by Article 9 Sub Article 1 of the Proclamation;

4/ **"Primary Pool"** means a first-level pool established at the Woreda, Zonal, or Regional level or similar level pools found at the City Administration level where members' contribution is deposited;

5/ **"Regional Pool"** means the highest level of pool in the Region, which is established by taking its share from primary pools; it also includes the primary Pool established at the Regional level;

6/ **"Primary Health Care Unit"** means a health post, health center, or a primary hospital, or any other health facility with similar status;

7/ **"Force Majeure"** means natural disaster or civil unrest or war, government order, or any other reason that is not foreseeable or preventable by the implementing body;

8/ **"Federal Implementing Body"** means Ethiopian Health Insurance Service pursuant to Article 7 Sub-Article (1) of the Proclamation;

፱/ **"የክልል አስፈጻሚ አካል"** ማለት በክልል ደረጃ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ሥርዓትን ለማስፈጸም በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚቋቋመው አካል ነው፣

፲/ በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## ስለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ቋት አመሠራረት እና የመጠባበቂያ ፈንድ

### ፫. የፌደራል ቋት ምሥረታ

የፌደራል ቋት ምክር ቤቱ በሚወስነው የቋት ክፍፍል ድርሻ መሠረት ከመሠረታዊ ቋቶች የሚያገኘውን የመዋጮ ድርሻ በመያዝ ይመሠረታል።

### ፬. ክልላዊ ቋት

፩/ ክልላዊ ቋት በክልል የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ምክር ቤት ውሳኔ ይመሠረታል።

፪/ ክልላዊ ቋቱ የሚመሠረተው ከመሠረታዊ ቋቶች የሚያገኘውን የመዋጮ ድርሻ በመያዝ ይሆናል።

### ፭. የቋት ክፍፍል ድርሻ አወሳሰን

፩/ የቋት ክፍፍል የሚደረገው በፌደራል ቋት እና በክልል ቋት መካከል ይሆናል።

፪/ የቋት ክፍፍል ድርሻ የሚወሰነው በየደረጃው ያለውን የጤና አገልግሎት ወጪ መጠን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የፌደራል ቋቱን ድርሻ ሲወስን በክልሎች መካከል ባለው የጤና አገልግሎት ተቋማት ስርጭት መሠረት የክፍፍል ምጣኔውን ሊለያይ ይችላል።

9/ **"Regional Implementing Body"** means a body established to implement Community-Based Health Insurance functions of the Region pursuant to Article 8 Sub-Article 1 of the Proclamation;

10/ Definitions in the Proclamation shall also apply to this Regulation.

## PART TWO

## Establishment of a Community-Based Health Insurance Pool and Reserve Fund

### 3. Federal Pool Establishment

The Federal Pool shall be established by taking its share from Primary Pools based on the Pool share determined by the Council.

### 4. Regional Pool

1/ The Regional Pool shall be established upon the decision of the Regional Community-Based Health insurance Council.

2/ The Regional Pool shall be established by taking its share from Primary Pools.

### 5. Principles for Allocating the Share of Pools

1/ Pool share is allocated between the Federal and Regional Pools.

2/ Pools share shall be allocated based on the health service expenditure at different levels of health facilities.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, when determining the share of the Federal Pool, the Council, may decide on a different Pool share percentage for some Regions by considering the distribution of health facilities in the Regions.

፬/ የፌደራሉ አስፈጻሚ አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፩ መሠረት የክፍፍል ምጣኔ ጥናት በማድረግ ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያስወስናል።

**፮. <u>የመጠባበቂያ ፈንድ አስተዳደር</u>**

፩/ በአዋጁ መሠረት የሚቀመጠው የመጠባበቂያ ፈንድ የሚውለው የፋይናንስ ጉድለትን ለመሸፈን ብቻ ይሆናል።

፪/ ምክር ቤቱ የመጠባበቂያ ፈንድ ድርሻን የሚወስነው የቋት ክፍፍል ድርሻ ምጣኔን መነሻ በማድረግ ይሆናል።

፫/ በፌደራል ደረጃ የሚቀመጠውን መጠባበቂያ ፈንድ የሚያስተዳደረው የፌደራሉ አስፈጻሚ አካል ይሆናል።

፬/ የክልሉን መጠባበቂያ ፈንድ የሚያስተዳድረው የክልሉ አስፈጻሚ አካል ይሆናል።

፭/ የክልል የመጠባበቂያ ፈንድ የሚቀመጠው በክልል አስተዳደር እርከን ብቻ ይሆናል።

፮/ የመጠባበቂያ ፈንድ ለዚሁ ተብሎ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ የሚቀመጥ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አባልነት፣ የአባልነት መዋጮ፣ የሃብት አሰባሰብ እና አስተዳደር</u>

**፯. <u>አባልነት</u>**

፩/ የአባልነት ምዝገባ የሚደረገው በአባወራው ወይም እማወራዋ ወይም በግለሰቡ መኖሪያ አካባቢ ሆኖ ከሚከተሉት ማስረጃዎች አንዱን ሲያቀርብ ይሆናል፡-

ሀ/ የቀበሌ ነዋሪነት መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት፣

ለ/ የመንጃ ፈቃድ፣ ወይም

ሐ/ በሚኖርበት አካባቢ አስተዳደር የተሰጠ የነዋሪነት ማረጋገጫ ደብዳቤ።

4/ The Federal Implementing Body shall conduct a study on Pools' share allocation and present it to the Council for approval.

**6. <u>Reserve Fund</u>**

1/ The reserve fund shall only be used to cover a financial deficit.

2/ The Council shall use the same proportion as the Pools' share when determining the proportion of reserve funds between the Federal and Regional Pools.

3/ The Federal Implementing Body shall administer the Federal reserve fund.

4/ The Regional Implementing B ody shall administer the Regional reserve fund.

5/ The Regional reserve fund shall only be deposited and managed at the Regional level.

6/ Reserve funds shall be deposited in a separate bank account.

## <u>PART THREE</u>

## <u>Community-Based Health Insurance Membership, Membership Contribution, Fund Collection, and Management</u>

**7. <u>Membership</u>**

1/ Membership registration shall be made by the household head or a single individual's residence upon receipt of one of the following proof of residency:

a) kebele identification card or a passport;

b) driving license;

c) a letter from the Government Administration proving residence.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም በንዑስ አንቀጹ ከተዘረዘሩት ማስረጃዎች ሁሉንም ማቅረብ ያልቻለ ሰው ምዝገባ በሚደረግበት አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ሶስት ግለሰቦች በሚሰጡት ምስክርነት ወይም በገጠር አካባቢ ማንነት ሊረጋገጥበት በሚችል በሌላ መንገድ በማረጋገጥ እና ቃለ-ጉባዔ በመያዝ ምዝገባ ሊደረግ ይችላል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በቤተ እምነቶች ወይም በጎዳና ላይ የሚኖር ሰው የክልል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ወይም እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች በተመለከተ ኃላፊነት የተሰጠው የክልሉ አካል የአባልነት መዋጮ በመሸፈን እና አስፈላጊውን ማስረጃ በመስጠት እንዲመዘገብ ያደርጋል።

**፰. <u>የአባልነት ምዝገባ ጊዜ</u>**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው የሁለት ተከታታይ ወር የአባላት ምዝገባ ወይም እድሳት ጊዜ ከመስከረም ፩ እስከ የካቲት ፴ ባለው ጊዜ ውስጥ ይከናወናል።

፪/ የክልሉ አስፈጻሚ አካል ለክልሉ ሁሉም አካባቢዎች የሚያገለግል አንድ የምዝገባ ወቅት ይወስናል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ አስፈጻሚ አካል በክልሉ የተለየ ገቢ ማግኛ ጊዜ ላለው አካባቢ የሚሆን ሌላ የምዝገባ ወቅት ሊወስን ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውጪ የአባላት ምዝገባ ወይም እድሳት ማድረግ አይቻልም።

2/ Without prejudice of Sub-Article (1) of this Article, persons without any documents can be registered based on the testimonies of three individuals that have permanent residence in the Kebele where registration is carried out, and this event shall be recorded in the minutes.

3/ Without prejudice to Sub-Article (1) and (2) of this Article, the Regional Bureau of women and social affairs or any other body entrusted with issues related to individuals residing inside and around places of worship and those who are homeless shall issue relevant documents, pay the membership fee and get them registered for membership.

**8. <u>Enrollment Period</u>**

1/ The two-month-long Community-Based Health Insurance enrollment and renewal period prescribed under Sub-Article (2) of Article 14 of the Proclamation shall range from Meskerem 1 to Yekatit 30.

2/ The Regional implementing body shall determine a single enrollment period that applies to all Regional areas.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the Regional implementing body shall set a second enrollment period for areas with different income generation periods.

4/ It shall not conduct membership enrollment and renewal outside the period proveded in this Article.

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ ድንጋጌ ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ምዝገባውን በወቅቱ ማከናወን ወይም ማጠናቀቅ ያልቻለ የወረዳ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አስፈጻሚ አካል የክልሉን አስፈጻሚ አካል በማሳወቅ ሲፈቀድለት ሊቀይር ወይም ሊያራዝም ይችላል፣ ሆኖም የሚራዘምበት ጊዜ የክልል አስፈጻሚው አካል ከወሰነበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ ከሰላሳ (፴) ተከታታይ ቀናት መብለጥ አይኖርበትም።

፮/ በዚህ አንቀጽ ከተፈቀደው የአባላት ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ውጪ ምዝገባ ወይም እድሳት ያደረገ የክልል አስፈጻሚ አካል ከጊዜ ገደቡ ውጪ ለሰበሰበው መዋጮ አጠቃላይ ድጎማ አያገኝም።

፯/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በኋላ ምዝገባ ወይም እድሳት የቀጠለ የክልል አስፈጻሚ አካል የፋይናንስ ጉድለት ቢያጋጥመው ከመጠባበቂያ ፈንድ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም።

**፱. <u>የአባልነት መዋጮ</u>**

፩/ የአባልነት መዋጮ መጠን የፌደራሉ አስፈጻሚ አካል በሚያደርገው ጥናት መነሻነት ለምክር ቤቱ ቀርቦ ይወሰናል።

፪/ ምክር ቤቱ የመዋጮ መጠን ሲወስን ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የቤተሰብ አባል የሚወስነው ዓመታዊ የመዋጮ መጠን ለመሠረታዊ ቤተሰብ አባላት እንዲከፈል ከተወሰነው መዋጮ ከአንድ አምስተኛ (፩/፭) ያነሰ መሆን የለበትም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) እና (፪) መሠረት የተወሰነው የአባልነት መዋጮ መጠን እንደአስፈላጊነቱ በምክር ቤቱ ክለሳ ሊደረግበት ይችላል።

5/ Without prejudice to Sub-Article (4) of this Article, a Woreda implementing body that cannot conduct or complete membership enrollment due to force majeure may change or extend the enrollment period upon approval by the Regional implementing body; The enrollment extension shall be counted from the date of decision by the Regional implementing body and, under any circumstances, shall not be more than thirty (30) days.

6/ A Regional implementing body that conducts enrollment outside the period specified in this Article shall not receive a general subsidy for the collection made outside the specified period.

7/ A Regional implementing body that continues enrollment after the period specified in this Article shall not benefit from the reserve fund.

**9. <u>Membership Contribution</u>**

1/ The Council shall determine membership contribution based on a study presented by the Federal implementing body.

2/ The contribution amount determined by the Council for additional family members shall not be less than one-fifth (1/5) of the contribution determined for the basic family.

3/ The membership fee determined as per Sub-Article (1) and (2) of this Article shall be revised as needed.

## ፲. የጤና ተቋማት የክፍያ ስልት እና ተመን

፩/ በጤና አገልግሎት ተቋማት ለሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች የተለያዩ የክፍያ ስልቶች ሊተገበሩ ይችላሉ።

፪/ የክፍያ ተመን የጤና አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ሊያመጣ በሚችል መልኩ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ይሆናል።

፫/ የጤና አገልግሎት የክፍያ ስልት እና የክፍያ ተመን በፌደራል ደረጃ በጤና ሚኒስቴር እና በፌደራል አስፈጻሚ አካል፤ እንዲሁም በክልል ደረጃ በክልል የጤና ቢሮ እና በክልሉ አስፈጻሚ አካል መካከል በሚደረግ የጋራ መግባባት የሚወሰን ይሆናል።

፬/ ከግል የጤና አገልግሎት ተቋማት ለሚደረግ የጤና አገልግሎት ግዢ ክፍያ የሚደረግበት ስልት እና ተመን በመንግስት የግዢ ሥርዓት የሚመራ ሆኖ በፌደራል ወይም በክልል አስፈጻሚ አካል እና በጤና ተቋሙ መካከል በሚደረግ የውል ስምምነት ይወሰናል።

## ፲፩. የመዋጮ እና ገቢ አሰባሰብ

፩/ የአባላት መዋጮ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ህጋዊ ደረሰኝ ተሰብስቦ ወደ መሠረታዊ ቋት የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም አባሉ መዋጮውን በቀጥታ ወደ መሠረታዊ ቋት የባንክ ሂሳብ ገቢ ሊያደርግ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት ተሰብስቦ ገቢ ለተደረገ መዋጮ ህጋዊ ደረሰኝ ይሰጣል።

## 10. Provider's Payment Mechanisms

1/ Various provider payment mechanisms will be adopted to effect payment to health facilities.

2/ The providers' payment mechanism under the Community-Based Health Insurance System aims at promoting the quality of health services and the equitable allocation of resources.

3/ The provider's payment mechanism and payment rate at the Federal level shall be determined based on a consensus between the Ministry of Health and the Federal Implementing Body and at the Regional level between the Regional Health Bureau and the Regional Implementing Body.

4/ The method and rate of payment for purchasing health services from private providers shall be governed by the existing Government procurement procedures and determined by a contractual agreement between the respective implementing body and the private provider.

## 11. Contribution and Income Collection

1/ Membership contributions shall be collected using official receipts and deposited to the Primary Pool's bank account.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, members can directly deposit membership contributions to the Primary Pool's bank account.

3/ Official receipts shall be issued to contributions collected and deposited per Sub-Article (1) and (2) of this Article.

፬/ የክልሉ አስፈጻሚ አካል ለተቀበለው አጠቃላይ ድጎማ የገቢ ደረሰኝ መቁረጥ ይኖርበታል።

፭/ የመዋጮ እና ገቢ አሰባሰብ ሥራ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል።

**፲፪. ገቢን ስለማስተላለፍ**

፩/ የክልሉ አስፈጻሚ አካል በምክር ቤቱ የተወሰነውን የፌደራል ቋት የመዋጮ እና የመጠባበቂያ ፈንድ ድርሻ የአባላት የምዝገባ እና እድሳት ጊዜ በተጠናቀቀ በአርባ አምስት (፵፭) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ወደ ፌደራል ቋቱ ማስተላለፍ ይኖርበታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የፌደራሉ አስፈጻሚ አካል የፌደራል ቋቱን የመዋጮ እና የመጠባበቂያ ፈንድ ድርሻ ከአጠቃላይ ድጎማው ላይ ቀንሶ ሊያስቀር ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚተላለፈው የፌደራል ቋት የመዋጮ እና የመጠባበቂያ ፈንድ ድርሻ የሚሰላው በዓመቱ ውስጥ የተሰበሰበውን መዋጮ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፬/ የተናጠል ድጎማ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ውስጥ መተላለፍ ይኖርበታል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ የተናጠል ድጎማ በጀቱን ማስተላለፍ ካልተቻለ የምዝገባና እድሳት ጊዜ በተጀመረ በሰላሳ (፴) ተከታታይ ቀናት ውስጥ መተላለፍ ይኖርበታል።

፮/ አጠቃላይ ድጎማ ለክልሉ አስፈጻሚ አካል የሚተላለፈው ከሐምሌ ፩ እስከ ነሐሴ ፴ ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

4/ The Regional Implementing Body shall issue an official receipt for the received general subsidy.

5/ The contribution and income collection may be digitalized.

**12. Transfer of Funds**

1/ The Regional Implementing Body shall transfer the share of the Federal Pool and reserve fund to the Federal Pool within forty-five (45) consecutive days following the completion of the enrollment and renewal period.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the Federal Implementing Body can deduct and retain its share of the Pool and reserve fund from the general subsidy due for the respective Region.

3/ The Pool and reserve fund share shall be calculated based on the annual contribution collected.

4/ The budget set aside for targeted subsidy shall be transferred to the Pool within the first quarter of the fiscal year.

5/ Without prejudice to Sub-Article (4) of this Article if the targeted subsidy is not transferred within the time frame, it shall be transferred within thirty (30) consecutive days following the commencement of the enrollment and renewal period.

6/ General subsidy shall be transferred to the Regional Implementing Body from Hamle 1 to Nehassie 30.

፯/ የክልሉ አስፈጻሚ አካል የአጠቃላይ ድጎማውን ስለመቀበሉ ድጎማው በደረሰው በሰላሳ (፴) ተከታታይ ቀናት ውስጥ የገቢ ደረሰኝ ቆርጦ መላክ ይኖርበታል።

፰/ በተለያየ ደረጃ ባለ ቋት መካከል ገቢ የሚተላለፍበት የአሠራር ሥርዓት አማራጭ አተገባበር እና በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ የሚከናወንበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይችላል።

፱/ የፌደራል ወይም የክልል አስፈጻሚ አካል በመንግስት የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት መሠረት የተሟላ እና ትክክለኛ የቋት የገቢና ወጪ መረጃ እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርቶችን መያዝ ይኖርበታል።

## ፲፫. <u>የፋይናንስ ጉድለት አሸፋፈን</u>

፩/ የፋይናንስ ጉድለትን ለመሸፈን ከመጠባበቂያ ፈንድ ወጪ ሆኖ ሊከፈል የሚችለው ያጋጠመው የፋይናንስ ጉድለት በፌደራል ደረጃ በፌደራል አስፈጻሚው እንዲሁም በክልል ደረጃ እንደአግባብነቱ በክልል አስፈጻሚው ወይም በክልል የፋይናንስ ቢሮ ሲረጋገጥ ይሆናል።

፪/ በየደረጃው ያለ ቋት ከመጠባበቂያ ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆነው፡-

ሀ) ጉድለት ባጋጠመበት የበጀት ዓመት በቋቱ ያለው የተጠራቀመ ጠቅላላ ገንዘብ ወጪውን መሸፈን ያልቻለ እንደሆነ፤ እና

ለ) ገቢውን በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ለተደነገገው ዓላማ ብቻ የተጠቀመ ሲሆን ነው።

፫/ የመጠባበቂያ ፈንድ ከመቋቋሙ በፊት የነበረ የፋይናንስ ጉድለት ከመጠባበቂያ ፈንድ አይሸፈንም።

7/ The Regional Implementing Body shall issue an official receipt within thirty (30) consecutive days of confirming receipt of the general subsidy.

8/ Transfer of funds within different-level Pools may be implemented through alternative mechanisms and ultimately digitalized.

9/ The Federal or Regional Implementing Body shall keep complete and accurate books of account mandated by the standard Government accounting procedures.

## 13. <u>Coverage of Financial Deficit</u>

1/ A financial deficit may be covered from the reserve fund after the Federal Implementing Body or at the Regional level when the Regional Finance Bureau or the Regional Implementing Body ascertains the validity of the financial deficit.

2/ Pools shall be eligible to benefit from the reserve fund if:

a) when the previously accumulated total Pool's fund is not enough to cover expenses in the fiscal year in which the financial deficit occurred; and

b) when the Pool's Administration used its income only for the purposes stipulated under Article 18 of the Proclamation.

3/ The reserve fund shall only cover the finical deficits that occurred after its establishment.

፬/ ቋቱ የፋይናንስ ጉድለት ያጋጠመው ገቢውን በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ከተጠቀሰው ዓላማ ውጪ በመጠቀሙ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ጉድለቱን የሚሸፍነው ቋቱ የተመሠረተበት የአስተዳደር እርከን ይሆናል።

**፲፬. <u>የቋት ወጪ</u>**

፩/ የቋት ወጪ ለጤና አገልግሎት እና ለጥቃቅን ወጪዎች የሚፈጸም ክፍያ ሲሆን አስተዳደራዊ እና የሥራ ማስኬጃ ወጪን አይጨምርም።

፪/ የጥቃቅን ወጪዎች ክፍያ ከቋቱ የሚፈጸመው በመሠረታዊ ቋት ደረጃ ብቻ ይሆናል።

፫/ የመሠረታዊ ቋቱ አስተዳደር ለሚከተሉት ተግባራት የሚያስፈልገውን ክፍያ ለጥቃቅን ወጪዎች በሚል ከተወሰነው ገንዘብ ላይ ሊሸፍን ይችላል፡-

ሀ) የአባላት መታወቂያ ህትመት፤ ወይም

ለ) በቀበሌ ደረጃ ላሉ መዋጮ ሰብሳቢ አካላት የሚከፈል ክፍያ።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፲፭. <u>ቀጥታ ክፍያ</u>**

፩/ የቀጥታ ክፍያ የሚደረገው በመጀመሪያ ደረጃ አሃድ የጤና ተቋም ብቻ ሲሆን የሚጠየቀውም ከተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አፈጻጸም የቅብብሎሽ ሥርዓቱን ተከትለው የሚሄዱ፣ የህክምና ቀጠሮ ታካሚዎችን፣ የድንገተኛ ታካሚዎች ወይም መክፈል የማይችሉ አባላትን አይመለከትም።

፫/ የቀጥታ ክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ የሚደረገው ምክር ቤቱ በሚወስነው ጊዜ ይሆናል።

4/ The administrative body where the Pool is established will cover the financial deficit when it has been determined that the funds are used contrary to the purposes stipulated under Article 18 of the Proclamation.

**14. <u>Pool Expenses</u>**

1/ Health services and miscellaneous costs are considered Pool expenses while Administrative and operational costs do not qualify as Pool's expenses.

2/ Expenses for miscellaneous costs shall only apply to the Primary Pool.

3/ The Primary Pool's administration may use miscellaneous expenses to cover the following costs:

a) printing of membership ID;

b) paying an incentive for membership contribution collectors at kebele level.

## <u>PART FOUR</u>
## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**15. <u>Co-Payment</u>**

1/ Co-payment shall only apply to outpatient services at the primary healthcare level.

2/ Beneficiaries who adhere to the referral system, patients on medical appointments, emergency patients, and indigents are exempted from co-payment.

3/ The co-payment system shall commence upon the decision of the Council.

**፲፮. <u>የመድኅን ሽፋን ገደብ</u>**

፩/ ለተጠቃሚው በዓመት የሚሸፈነው የመድኅን ሽፋን የአይነት ወይም የገንዘብ መጠን ወይም የሁለቱም ገደብ እንዲኖረው ሊደረግ ይችላል።

፪/ ምክር ቤቱ የመድኅን ሽፋን ገደቡን ይወስናል።

፫/ በምክር ቤቱ የሚወሰነው የመድኅን ሽፋን ገደብ የጥቅም ማዕቀፉ አካል ይሆናል።

**፲፯. <u>የመረጃ አያያዝ እና ሪፖርት አቀራረብ</u>**

፩/ የመሠረታዊ ቋት አስተዳደር የተሰበሰበውን የመዋጮ መጠን፣ የአባላት እና የተጠቃሚዎችን ዝርዝር መረጃና የጤና አገልግሎት አጠቃቀም ሁኔታ እንዲሁም ለጤና አገልግሎት ተቋማት የተከፈለ ገንዘብ መረጃ አደራጅቶ መያዝ ይኖርበታል።

፪/ ከመሠረታዊ ቋት በላይ ያለ የቋት አስተዳደር የአባላት እና ተጠቃሚዎችን ብዛት እና የጤና አገልግሎት አጠቃቀም መረጃ እንዲሁም የተሰበሰበውን አጠቃላይ የገንዘብ መጠን እና የክፍያ መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝ ይኖርበታል።

፫/ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱ ሰነዶች በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ የሚቀመጡበት ሥርዓት ይዘረጋል።

፬/ በየደረጃው ያለ አስፈጻሚ አካል ወቅታዊ፣ ትክክለኛ እና የተሟላ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

**፲፰. <u>በሶስተኛ ወገን የሚሠሩ ተግባራት</u>**

፩/ የፌደራሉ ወይም የክልሉ አስፈጻሚ አካል የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን ሥራን በሶስተኛ ወገን የሚያሠራው የሚከተሉትን ነጥቦች ታሳቢ በማድረግ ይሆናል፡-

ሀ) ሥራውን በተሻለ ጥራት ለማሠራት ሲያስፈልግ፣ ወይም

ለ) ሥራዎችን በተሻለ ቅልጥፍና ለማሠራት ሲያስፈልግ፣ ወይም

**16. <u>Capping</u>**

1/ The annual health service coverage for beneficiaries may be capped based on the type or total expenditure or both of health services.

2/ The council shall decide the amount of expenditure of capped health services.

3/ The capped health services that decide by the Council shall be part of the benefits package.

**17. <u>Data Management and Reporting</u>**

1/ The Primary Pool's Administration shall keep records of the total contributions, a list of members and beneficiaries, health service utilization, and payments made to health facilities.

2/ Pool's Administration above the Primary Pool shall keep a proper record of the list of members and beneficiaries, the total amount of contribution collected, health service utilization, and other payment-related data.

3/ The data management and reporting system may be digitalized.

4/ Implementing Bodies at various levels shall submit timely, accurate, and complete reports.

**18. <u>Outsourcing</u>**

1/ The Federal or Regional Implementing Bodies shall consider the following when outsourcing activities:

a) to ensure a better quality of work; or

b) to get the job done more efficiently; or

ሐ) በሶስተኛ ወገን ማሠራት ወጪን የሚቀንስ ሆኖ ሲገኝ ነው።

፪/ የፌደራሉ ወይም የክልሉ አስፈጻሚ አካል የሚከተሉትን ተግባራት በየደረጃቸው በተቋቋመ የሥራ አመራር ቦርድ በማስወሰን በሶስተኛ ወገን ሊያሠራ ይችላል፡-

ሀ) የመዋጮ አሰባሰብ ሥራ፣ ወይም

ለ) የመታወቂያ ዝግጅት ወይም ስርጭት፣ ወይም

ሐ) የክፍያ አስተዳደር ወይም የህክምና አገልግሎት ጥራት ኦዲት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ሀ) እና (ለ) ላይ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተደነገገው መሠረት ክፍያው ከጥቃቅን ወጪዎች ሊሸፈን ይችላል።

**፲፱. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**፳. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፩ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

c) when it is determined that outsourcing could result in cost reduction.

2/ The Federal or Regional Implementing Body may outsource the following activities upon approval of their Management Boards:

a) membership fee collection;

b) id preparation or distribution; or

c) claim management or medical audit.

3/ Payment for services under Sub-Article 2 (a) and (b) of this Article shall be covered from miscellaneous expenses per Sub-Article 3 of Article 14 of this Regulation.

**19. Non-Applicable Laws**

Any Regulation, Directive, or customary practice inconsistent with this Regulation shall have no effect on matters covered in this Regulation.

**20. Effective Date of the Regulation**

This Regulation shall enter into force upon the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 9th Day of May, 2023.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**